**ለህዝቡስ መዳን ከሌላ ስፍራ ይመጣላቸዋል እርስዎ ግን……**

ይድረስ ለዶክተር አብይ!

በአዲስ ተስፋ

addiste@gmail.com

ለመነሻ እርስዎ ከሚያውቁት ታላቁ መጽሐፍ በተወሰደ ታሪክ ልንደርደር። እነደሚያውቁት  አስቴር ፣ መርደኪዮስና ሃማ ስለሚባሉ  ስዎች ታሪክ **በመጽሓፈ አስቴር** ተመዝግቦ ይገኛል። ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ ያሉትን አንድ መቶ ሃያ ሰባት አገሮች ይገዛ የነበረው የንጉስ ጠረክሲስ ባለቤት የሆነችው ንግስት አስጢን ንጉሱ ክብሯ ለህዝብ እንዲታ ሲፈልግ ፈቃደኛ ባለመሆኗ በጣም ተቆጣና በወቅቱ በነበረው ህግ መሰረት የንግስቲቱን ቦታ አይሁዳዊቷ አስቴር ወሰደችው። ስለዚህም **አስቴር ንግስት ሆነች**።አስቴር መርደኪዮስ እንደ ልጁ አድርጎ ያሳደጋት የአጎቱ ልጅ ነበረች። መርደኪዮስ ደግሞ በንጉሱ ላይ ክፉ ያስቡ የነበሩ ሰዎችን እቅድ በመስማቱ  ንጉሱን ከሞት ያዳነ ባለውለታ ነበረ። ይህ ሰው ለፈጣሪው እንጅ ለሰው ባለመስገዱ የንጉሱ የቅርብ ሹም ሃማ አይሁዳዊውን መርደኪዮስን ለማጥቃት ተነሳ። ከዚህም የተነሳ የመርደኪዮስን ወገን አይሁድን በሙሉ እንዲጠፋ የሚያደርግ አዋጅ ከንጉሱ እንዲታወጅ አደረገ። አይሁድ ሁሉ መርደኪዮስን ጨምሮ የሚገድልበት አዋጅ ታወጀ። በዚህ ጊዜ ነበር መርደኪዮስ የንግስቲቱን የአስቴርን ርዳታ በመጠየቅ አዋጁ እንዲገለበጥ ያደረገው። መርደኪዮስ  አስቴር  መጫወት ስለሚገባት ሚና አጠንክሮ ከነገራት በኋላ የሚከተለውን መልዕት ላከላት። አንቺ በንጉስ ቤት በመሆንሽ ብቻ ሌላው የአይሁድ ህዝብ ሲጠፋ አንቺ የምትተርፊ እንዳይመስልሽ። በዚህ ጊዜ አንቺ ዝም ብትይ **ለአይሁድ መዳን ከሌላ ስፍራ ይመጣላቸዋል**፣አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ ፤ደግሞስ አንቺ ንግስት ለመሆን የበቃሽው ለዚህ ጊዜ እንደሆነ ማን ያውቃል? በማለት አስጠነቀቃት።

ይህንን ታሪክ የማነሳው እርስዎ በደንብ የሚያውቁት ታሪክ ስለሆነ ነው። መርደኪዮስ ምንም እንኳ አስቴር ያሳደጋት ዘመዱ ብትሆንም  በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ማድረግ ስለሚገባት ተግባር በማስጠንቀቂያ አመለከታት። እርሷ ባትቀበልና የራሷን ድርሻ ባትወጣ ግን **መዳን ለአይሁድ ከሌላ ስፍራ እንደሚመጣላቸው** ጭምር ተናገረ። ለአይሁድ መዳን  አስቴር ብቻ ብቸኛ መንገድ አልነበረችም። አይሁድ አዋጅን በወራትና በቀናት መካከል ብቻ ሳይሆን በሰዓታት ልዩነት የሚያስገለብጥ ፈጣሪን ያመልካል። ስለዚህም አስቴር የራሷን ድርሻ ባትዎጣ ወዮላት።

ክቡርነትዎ የኢትዮጵያ ህዝብ **ኢትዮጵያ** በማለትዎ ብቻ ዘርዎን ፣ የቀደመ ፖለቲካ አመለካከትዎን፣ እድሜዎንና ሃብትዎን ሳይመለከት ሆ ብሎ ደገፈዎት ። በሚያስገርም ፍጥነትም የእርስዎን ሞት ለመሞት ራሱን ሰጠዎት። ለእርስዎ የተዎረወረ ቦምብ ማክሸፊያ እግሩንና አካሉን ለመስጠት ህይዎት አላጓጓቸውም። ዛሬ  ያለምንም ማስረጃ መፈንቅለ መንግስት አደረጉብኝ ብለው የዎነጀሏቸውና ያስገደሏቸው ብርጋዴር ጀነራል አሳምነው ጽጌ ሳይቀሩ **የኢትዮጵያውያን ሙሴ** ብለው እንደጠሩዎት ያውቃሉ።ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምስራቅ እስከ ምእራብ  የእርስዎ ድርጅት በዘርና በጎጥ እንደ በታተነው ሳይሆን አንድ ሆኖ አጋርዎ ለመሆን ቃል ገባ። እርስዎ የሚያደርጓቸውን ዲስኩሮች ሙሉ በሙሉ በማመንም ከሴራ ፖለቲካ የጸዳ፣ እኩልነትና ፍትህ የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊትና በቀደመ ክብሯ ገናና የሆነች ኢትዮጵያን ተስፋ አደረገ። ታላቋን ኢትዮጵያን እያቀነቀኑ በርካታ እጸጾችን ሲፈጽሙ እያየ እንኳ በተቃውሞ ሊያሸማቅቅዎ አልሞከረም። በርካታ ከሆኑትና የሴራ ፖለቲካ ቀጣይ አካል ከሆኑት ውሳኔዎችዎና እንቅስቃሴዎችዎ ጥቂቶችን ብንመለከት

- የአዲስ አበባን ቻርተር አንዲት አንቀጽ ቀይሮ **አቦ ታከለ ኡማን** ከንቲባ ለማድረግ የፈጀብዎት አንዲት ሌሊት ብቻ መሆኑ ሳይሆን ከንቲባ የመሆን መብት የነበራቸውን ወይዘሮ በጥበብ ከአዲስ አበባ ምክር ቤት እንዲዎጡ ያደረጉበት መንገድ
- እርስዎ መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ መጡ ያሏቸውንና ፑሽ አፕ አብረው በመስራት የሸኟቸው የሰራዊቱን አባላት እንዴት እንደመለሱ ሲናገሩ በዘዴ ባንመልሰው ኖሮ መንግስቴ ሊገለበጥ ነው ብለው ከሰበታ፣ ቡራዩ፣ ሱልልታና ከፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን በርካታ ጦር ወደ ቤተመንግስት በመምጣት ላይ ነበር በማለት የእርስዎ ደጋፊ ጠባቂና አለኝታ የመጡበት ነገድ ብቻ እንደሆነ የገለጹበት መንገድ ሆ ብሎ ከጫፍጫፍ የደገፈዎትን ኢትዮጵያዊ አሳዛኝ ነበር
- የቀድሞው ህወሃት መራሽ ኢህአዴግ ለራሱ ጥቅም እንዲመቸውና ነገዱ መደበቂያ እንዲሆነው የተቀረውን የትግራይ ህዝብ በሌላው ኢትዮጵያዊ እንዳይታመንና እንዳይተማመን እንዳደረገ ሁሉ እርዎም የኦሮሞን ህዝብ ከሌላው ጋር መነጣጠሉ እንዲበረታ የሄዱበት ርቀትና( እዚህ ላይ አምስቱ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶችና የእርስዎ ፓርቲ ኦዴፓ ስለ አዲስ አበባ ያወጡትን መግለጫ መጥቀስ ይቻላል)ኦነግ ላይ ያለዎት ከልክ ያለፈ መለሳለስ
- በቡራዩ በተፈጠረው አለምን ባስደነገጠ የዜጎች መፈናቀል ላይ በሰጡት አስተያየት እኔ ስለ እቅዱም ሆነ አፈጻጸሙ የማውቀው ነገር አልነበረም የሚል ቀልድ
- በጌድዮና ጉጂ ዞኖች በተፈጸመው ግጭት የተፈናቀሉትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ህይዎት ሳያሰስብዎ መረጃው ለአለም አቀፍ የሚዲያ አውታሮች ከተሰራጨና አንዳንድ አገር ወዳድ ግለሰቦች የዜጎችን ህይወት ለመታደግ በቀናት ወስጥ በርካታ ሚሊየን ብር በመሰብሰባቸው የተሰማዎትን ቁጭት ለመግለጽ እነዚያን በጎ አድራጊዎች ከማመስገን ይልቅ ነጋዴዎች በማለት ለማሸማቀቅ የሄዱበት ርቀት
- የኢንጅነር ስመኘውን ግድያ ማጣራት ጉዳይ ያሳዩት ቸልተኝነት
- ጀሮ በሚሰቀጥጥ መልኩ ከአስራ ስምንት እስከ ሃያ የሚደርሱ ባንኮች ተዘርፈው እያለ ስለሁኔታው ምንም ያለማለትዎ
- በሃገራችን ያሉት መንግስታት ሁለት ናቸው፤ እኔ የምመራውና አብይ የሚመራው ተብሎ በአደባባይ ሲነገር ተጠያቂነት እንደሌለ ሰዎች እንዲያስቡ በማድረግ ያሳዩት ቸልተኝነት
- አማራ ክልል ፤በጎንደር ፤ወሎ ከሚሴ፣ ሰሜን ሸዋ እንዲሁም ቤንሻንጉል ጉምዝ ፣ ኦሮምያ፣ትግራይና አማራ ክልል አጎራባች ቦታዎች በተነሳው ግጭት ጥፋተኞችና ተንኳሾች እየታወቁ ሆን ተብሎ የፖለቲካ ስራ ሲሰራ ምንም አይነት ርምጃ ለመውሰድ ፈቃደኛ አለመሆንዎ የሀገራችንን ማህበራዊ እሴት በናደ መልኩ ግለሰቦች ተነስተው አንድ ዘር ከሌላው ነገድ ጋር መጋባቱ ቋንቋን ይገድላል በማለት የህብረተሰባችንን አብሮ የመኖር ዘመን ተሻጋሪ እምነት በጥላቻ ለመናድ ሲሞክሩ በህግ እንደሚጠየቁ እንኳ ያለመነገሩ አደገኛነት
- እና በርካታ ስህተቶችዎን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለመቁጠር አቅቶት ሳይሆን ታላቅ ስላሏት ኢትዮጵያ በነበረው እምነት ሊቃወምዎ አልወደደም ነበር። አንድ ነገር ልነግርዎ እወዳለሁ፤ እርስዎ የህዝቡን እምነት **ቢጥሉትም ለኢትዮጵያውያን መዳን ከሌላ የመጣላቸዋል።** ለእርስዎ ግን ይህ ታላቅ እድል ብቻ ሳይሆን በታሪክ ሃላፊነትዎን የሚዎጡበት ወርቃማ ጊዜ ነበር። እርስዎን የሚያክል ሰው ስኬቱን አንድ ሁለት እያለ እየቆጠረና ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የሆኑ ሁሉ የሚሰጥዎትን ማሞካሸት በመቀበል መልካም እያደረጉ ያሉ ከመሰለዎት በጣም ተሳስተዋል። በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከመቸውም በከፋ መልኩ ተከፋፍለዋል። በእርግጥ በመጽሃፍዎ እንዳስቀመጡት ስልጣንን ለማጠንከር ሁለት ተቃዋሚ ቡድኖች መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል። ነገር ግን ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት እርስዎ የአስቴርና መርደኪዮስን ታሪክ በደምብ ያውቃሉ።

እንደነገርኩዎት ስለ በርካታ እጸጾችዎ ለማውራትና በደልዎን ለመቁጥር ሳይሆን ያመነዎትን የኢትዮጵያ ህዝብ በመርሳትዎና አይን ያዎጣ አድሎአዊ አሰራርዎን ለመጠቆም የሚያውቁቱን ታላቅ መጽሓፍ ዋቢ በማድረግ ላሳይዎ ወይም የኢትዮጵያ ህዝብ በአጽኖት እየተመለከተዎ መሆኑን ለመጥቆም ስለዎደድኩ

ነው። **መላውን ያመነዎትን ህዝብ ቢጥሉ ግን ይሙኑኝ መዳን ለዚህ ህዝብ ከሌላ ስፍራ ይመጣለታል።**

በራሱ ነገድ የታወረውና በመንጋ ፍትህ የሚያምነው ዘውጌ በርጋታና በማስተዋል የህዝባችንን ጥያቄ በእኩል አይን ያለማዳላት በመመልከት ዲሞክራሲ ወይም ፍትህ ያመጣል የሚል እምነቱ ባይኖረኝም እርስዎ ግን ከነገድ፣ ከቋንቋና ከዘር በላይ በሰው ልጆች እኩልነት ያምናሉ የሚል እምነት ነበረኝ። ቢያንስ ከመጡበት ስፊ ማህበረሰብ እሴት ቀድተው እኩልነትን ያሰፍናሉ እንጅ አድልዎን በአደባባይ ይፈጽማሉ ተብሎ አይጠበቅም ነበር።

## የመንግስት ግልበጣ በአማራ ክልል

በስደት ከምኖርበት አለም የታመመች እናቴን ለመጎብኘት ሰኔ 15 ( ጁን 22 ) ቅዳሜ አዲስ አበባ ረፋዱ ላይ ገባሁ። የ 12 ሰዓት የአውሮጵላን በረራ ሰውነቴን አድክሞት ነበርና ወዳረፍኩበት ሆቴል በፍጥነት ሄድኩና ለማረፍ ተኛሁ። ወደ ምሽቱ 11 ሰዓት አካባቢ ስነሳና ቴሌቪዥን ስከፍት በአማራ ክልል የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተደረገ ያምትል ዓረፍተ ነገር ብቻ በተደጋጋሚ በቴለቪዥኑ መስኮት ይሰማ ነበር። የሞባይል ኔትወርክ ተቋርጧል፤ ኢንተርኔት አይሰራም። ደጋግሜ ዜናዋን ሰማኋት፣ አንዳች የተቀነባበረ ተንኮል ሸተተኝ። ዜናዋ ፍሬም የተደረገች ነች። በዚያ ላይ ሁሉም ቻናሎች እንደ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዩኒፎርም ተስተካክሎ የተሰጣቸውን አንድ አይነት አረፍተ ነገር ብቻ ነበር የሚያነብቡት። ራት በላሁና ተመልሼ ተኛሁ። በማግስቱ ስነሳ ይህችው ዓረፍተ ነገር የሞቱትን የዶክተር አምባቸውንና ፣ የደህንነት አማካሪያቸውን አቶ እዘዝ ዋሴን ስም በመጨማር መስዋዕት መሆናቸውንና ከአዲስ አበባ ደግሞ ጀነራስ ሳእረ ከጓደኛቸው ብ /ጀነራል ገዛኢ ጋር በመኖሪያ ቤታቸው መገደላቸውን ከመጨመር ሌላ ምንም የተለወጠ ነገር አልነበረም። መፈንቅለ መንግስት ተካሄደ የሚለው መሪ ዜናው ነበር ። ቆየት ብሎ የጠቅላይ ሚኒስቴሩ የፕሬስ ሴክቴሪያት ሹም ለሚዲያ መግለጫ ሰጡ። በአማራ ክልል መፈንቅለ መንግስት መካሄዱንና የመፈንቅለ መንግስቱ መሪም ጀነራል አሳምነው መሆናቸውን በእርግጠኝነት ተረኩ። ንጉሱ ጥላሁን ጀነራል አሳምነው ያቀነባበሩት መፈንቅለ መንግስት ሙሉ በሙሉ እንደከሸፈና ተባባሪዎችን አሳዶ ለመያዝም እየተሰራ መሆኑን ፌደራል ፖሊስና ፌደራል ወታደሮችም አስቀድመው መግባታቸውን አረዱ። ከዚያም ሁሉም ቻናሎች ይህችንኑ ብቻ ማስተጋባት ጀመሩ። አቶ ምግባሩ ገና አለመሞታቸው ይነገር ነበር። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ የመፈንቅለ መንግስት መሪ የተባሉት ብርጋዲየር ጀነራል አሳምነው ጽጌ መገደላቸው ተነገረ። ሌላው አደናጋሪ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ አስተዳደሩ እንደሚንቅ ያሳየበት ዜና ደግሞ ስለ ጀነራል ሳእረ አሟሟት አራት ጊዜ የተቀያየረው ዜና ነበር። ገዳያቸው ራሱን አጠፋ፣ ተገደለ ሆስፒታል ገብቶ እየታከመ ነው እና ሌላም ሌላም። በማግስቱ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ወጡና እንዲሁ በተቃጣው የመንግስት ግልበጣ በማለት መናገር ጀመሩ። እርስዎ የመንግስት ግልበጣ ካሉ በኋላ ደግሞ ተዋቀረ የተባለው አጣሪ ቡድን እያንዳንዱን ሪፖርቱን መፈንቅለ መንግስት ማለቱ ብቻ ሳይሆን አቀናባሪው ብርጋዴር ጀነራል አሳምነው ጽጌ በማለት ከቤተመንግስት የወጣውን ሃረግ ማስተጋባት ተያያዘው።በዚህን ጊዜ ትዝ ያሉኝ አቶ መለስ ዘናዊ ነበሩ። በየጊዜው የሚፈጥሯቸውና ፓርላማቸው ፣ተከታዮቻቸውና ካድሬዎቻቸው እንደገደል ማሚቶ የሚያስተጋቧቸው ቃላት።

የተከበሩ ዶክተር አብይ ወደ ሚቀጥለው ትንታኔ ከመሄዴ በፊት በዎንጀል መግለጫ አሰጣጥዎም ሆነ በፍጥነት መረጃ ሳያጣሩ በመስጠትዎ ትልቅ አድልዎ እንዳደረጉ ላስታውስዎ እፈልጋለሁ። በአራት ኪሎ ቤተመንግስት ቀጥታ እርስዎን ለመገልበጥ መጡ ያሏቸውን ወታደሮች( በቁጥር ብዙ) እንኳ እርስዎ በአካልና በግንባር እያወቁት መንግስት ግልበጣ ብለው መግለጫ አልሰጡም። እንዲያዉም እየተፍለቀለቁ ደሞዝ ጭማሬ ፈልገው ነው ሁሉ ሰላም ነው በማለት ተናግረው ነበር ሁኔታውን

ያረጋጉት። ከብዙ ቀናት በኋላ ፓርላማ ቀርበው ግን መፈንቅለ መንግስት ሙከራ እንደተደረገብዎ ነገሩን። ታዲያ የአማራ ክልልን የባለስልጣኖች ግድያ መፈንቅለ መንግስት ብለው ሲጠሩት ምነው እርግጠኛ ሆኑ? የፌደራል የጸጥታ ሃይሎችስ በማን ፈቃድ ነበር ወዲያውኑ የገቡት? ነው ወይስ በዐማራ ክልል የተካሄደው መፈንቅለ መንግስት በእርስዎ ሚኒሊክ ቤተመንግስት ከተደረገው ይበልጣል?

## እስኪ ስለ ዐማራ እንነጋገር

የፓርቲዎን ሰዎች(ኦዲፒ)ጨምሮ በርካታ ምሁራን ፖለቲከኞችና ማህበረሰብን በማንቃት ላይ የሚገኙ ግለሰቦች በዐማራ ህዝብ ላይ ከፍተኛ ፖለቲካዊ ሻጥር እንደተሰራና ሆን ተብሎ ህዝቡ በረሃብ ድህነትና ማይምነት ውስጥ እንዲኖር እንደተደረገ ይስማማሉ። እርስዎም ይህንኑ ያውቃሉ። በተለይ ሌላው ማህበረሰብ ዐማራን እንደ ጨቋኝና በዝባዥ አድርጎ እንዲቆጥረው የተሄደበት ርቀት አሳሳቢ መሆኑ ይታወቃል። ህውሃት የዚህን ሴራ ተግባራዊነት በመከታተልና በማስፈጸም የአንበሳውን ድርሻ የምትወስድ ቢሆንም ሌሎች ሻቢያንና ኦነግን የመሳሰሉ ጽንፈኛ ቡድኖች የትያትሩ ደራሲዎችም ተዋናዮችም ነበሩ። ምስኪኑ ዐማራም በነቂስ ወጥቶ የደገፈዎት ይህንን ሴራ ከተረዳና ጠላቶቹ እነማን እንደሆኑ ካወቀ በኋላ ነበር። ባለውለታዎ የሆነው ይህ ህዝብ ዛሬም በእርስዎ አገዛዝ ተጨቋኝና ኢፍት ሃዊ ተግባር የሚፈጸምበት ህዝብ ሆኖ ቀጥሏል። በመፈንቅለ መንግስት ተካሄደ ሰበብ በርካታ መሪዎቹ፣ ነጋዴዎች፣ መምህራንና የዐማራ ጥቅም መደፍጠጥ ያንገበገባቸው እውነቱን እያፍረጠረጡ ለሚዲያ ያደረሱና ንቁ ተሳታፊ ወጣቶች እስር ቤት በመጋዝ ላይ ይገኛሉ።በመፈንቅለ መንግስት ሰበብ እያስፈራዎት ያለውን የአብን አመራሮች አባላትና ደጋፊዎች ማሳደዱን ቀጥለውበታል።

ክልሎች ለምን ክፍተኛ በጀት ኖራቸው የሚል ጭፍን ቅናት ወይም ጥላቻ የለኝም። ፍትህን አሰፍናለሁ የሚሉት እርስዎ ራሱ እስኪ ይፍረዱ? በየትኛውና በምን መስፈርት ይሆን ከ5 ሚሊየን የማይበልጥ ነዋሪ ያላት ትግራይ አመታዊ በጀቷ ሃምሳ ቢሊየን ሲሆን ከሰላሳ ሚሊይን ህዝብ በላይ የሚኖርበት የዐማራ ክልል ግን 47 ቢሊዮን ሊሆን የሚችለው?ይህን ጽሁፍ እያዘጋጀሁ ወሎ ላሊበላ ደርሰው የተመለሱ በርካታ የዐማራ ወጣቶች አመራሮች ታሰሩ የሚል ዜና ሰማሁ።ሃረር ከተማን ውሃ አይደርሳትም በማለት ለወራት የህብረተሰቡን ሰላም ሲያውኩ የነበሩ የተደራጁ ወጣቶች ሲታሰሩ አልሰማንም ፤ ከጅቡቲ ሸቀጦችን ጭነው አዳማ የደረሱ የጭነት ተሽከርካሪዎችን እኛ ካልሆንን ማንም ማራገፍ አይችልም በማለት መኪኖችን ያገቱ ወጣቶች ሲታሰሩ አልሰማንም፤ ከየ አካባቢያቸው መጤዎች ይውጡ በማለት የዘጎችን ንብረት ሲዘርፉ ህይዎትም ሲያጠፉ የታዩ የተደራጁ ወጣቶች አልታሰሩም ፤ ነገር ግን በማንነታቸው ዐማራ የሆኑ የህዝባቸውን በደልና ጭቆና ለሌላው ማህበረሰብ የሚያሳውቁ ጋዜጠኞችም ሆኑ የወጣት አመራሮች የሚታሰሩበትና የሚሳደዱበት ምክንያት ምንድነው? ቀደም ብየ የትግራይንና የዐማራ የ2019/2020 ዓም በጀት ለማወዳደር ሞክሬ ነበር። ሌላ አንዲት ነገር ልጨምር።ኢትዮጵያ ካሏት የማኑፋችቱሪንግ ኢንደስትሪዎች

| | |
|---|---|
| አዲስ አበባ | 40% |
| ኦሮሚያ | 21% |
| ደቡብ | 13% |
| አማራ | 11% |
| ትግራይ | 9% |
| ድሬዳዋ | 2% |
| ሌሎች በጋራ | 4% |

ቤንሻንጉል፣ ሶማሊያ፣ ጋምቤላና አፋር በጋራ ያላቸው 4% ሲሆን የዐማራንም ስንመለከት ቁጥሩን የሚመጥን አይደለም ። አዲስ አበባ የኦሮሞ ነው የሚለውን ፖለቲካ ስንጨምርበት 61%

የማኑፋክቱሪንግ ኢንደስትሪ የሚገኘው የእርስዎ ፓሪቲ ግዛቴ ነው በሚለው አካባቢ ብቻ ነው ማለት ነው። መቼም ሁሉ የእኔ ነው የሚለው ልፈፋ በሌላው ኢትዮጵያዊ ላይ ምን ያክል የስነ ልቦና ጫና እያመጣ እንዳለ ጠንቅቀው ያውቁታል። **ታዲያ ኢፍትሃዊነት በእርስዎ ዘመንም እንዲቀጥል ለምን ፈቀዱ?**

በመሰረቱ እየሆነ ያለው ሁሉ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለማጥፋት ብቻ ሳይሆን ዐማራ የሚባልን ነገድ ከምድረ ገጽ መታሰቢያው እንዳይኖር ለማድረግ ቢያንስ የአስተዳደርዎ ዋና ዋና ሰዎች እየሰሩ እንደሆነ ለእርስዎ መንገር ለቀባሪው አረዱት ማለት ነው። ዐማራ ህገመንግስቱ ስለማይወክለኝ ይነሳልኝ በማለቱና ዶክተር አምባቸውም ይህንን ደጋግመው በመድረኮች ሁሉ ስላነሱት ለግድያቸው ዋና ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው። የአብን የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ ክርስቲያን ታደለ ውሃ በማይቋጥር ሁኔታ እንዲታሰር የሆነው እርስዎን በጠየቀውና በአደባባይ እርቃንዎን ባስቀረበበት ጥያቄ ምክንያት ነው። ሕገ መንግስቱ መሻሻል ይገባዋል ሲል በአንድ ስፈር ስዎች ምክንያት ህገ መንግስት አይሻሻልም በማለት ለዐማራ ህዝብ ያለዎን ንቀትና ጥላቻ በአደባባይ ገለጹ ፤ ይህም እርስዎን ከተቀባይነት ማማ አወረድዎት።
በዚህ ቂም የቋጠሩ ጋሻዣግሪዎችዎ የአብን አባላት፣ ደጋፊዎችና አመራሮች ማሳደዱን ተያያዙት። እንጅማ በስልጣን ዘመንዎ የከፋውን ወንጀል የሰራ እንደ ኦነግ ያለ ድርጅት የለም። ከቤንሻንጉል እስከ ጌድዮ፣ ከሶማሌ አጎራባች እስከ ሃረሪ፣ ከአማራ ኬሚሴ እእስከ አዲስ አበባ ከወለጋ እስከ ሰሜን ሸዋ ዜጎችን ያፈናቀለ ፣ የገደለና የዘረፈ ኦነግና ኦነግ ብቻ ነበር። በአዲስ አበባ ታላላቅ ሆቴሎች ከሚጦሩት መሪዎቹ ጀምሮ በጫካ ንጹሃንን እስከሚቀጥፉ ታጣቂዎቹ ድረስ አንድም ሊታሰር ወይም በህግ ሊጠየቅ የቻለ አልነበረም። ዐማራ ነጻነቱን ማግኘት አለበት ብለው ሃሳባቸውንና ተቆርቋሪነታቸውን ብቻ ያሳዩትን አብንና አባላቱን ግን ምክንያት እየተፈለገ ወደ እስር ቤት ማጋዝ ለእርስዎ ድጋፍ ለማድረግ ከጫፍ ጫፍ ለተንቀሳቀሰው አማራ ሽልማት ሆነ።

**ክቡርነትዎ የዐማራ ህዝብ መዳን ከሌላ እንደሚመጣለት አይጠራጠሩ** ።እርስዎ አሁን እያደረጉት ያሉት የዐማራ ህዝብ ቢነካ ምን ያመጣል? ልጆቹን ለመከላከል ኣጸፋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይስ የምናደርገውን ሁሉ ዝም ብሎ ይቀበላል? የሚል የእሳት ላይ ጨዋታ ነው። ዐማራ የእርስዎ ፓርቲ እደሚያደርገው ይህ የእኔ ነው ያ የእኔ ነው የሚል ሽሚያ ውስጥ አልገባም። ናዝሬት የእኔ ነች፣ ደብረዘይት የእኔ ነው ድሬዳዋን ቆርቅሬያለሁ ከወለጋ በግፍ ጠፍቻልሁና የእኔ ነው አላላም። **ዐማራ ያለው አገሩ ሁሉ የሁላችን ነው ፣ ሁላችንም በጋራ በእኩልነትና በነጻነት እንኑር እንጂ** አጎራ ዘለል የሆኑትና የማንነት ቀውስ ውስጥ እንዳሉት ህዝቄል ጋቢሳ ወሎ ጌዲዎ ሶማሊያ አፋር ቤንሻንጉል ጋምቤላ የእኔ ነው በማለት እንደ ተናካሽ ውሻ አፉን አልከፈተም። ዐማራ የበታችነት ስሜት እንዳዘቀጣቸውና ሁሌም ዐማራ ፎቢያ እንደሆኑት የተጋቡ መፋታት አለባቸው ቋንቋህን ካልተናገረ አባረው ሸቀጥህን አትሸጥለት እንደሚሉት በቀለ ገርባ አይነት ምሁር ነኝ ባይ መሃይም የለውም። ዐማራ አገር ሲሰራ ፣ ፍትህን በባህላዊ ሸንጎው ሲከውን የኖረ ለጠላቱ ሬት ለወዳጁ ደግሞ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ነገሮችን ሁሉ በትእግስት ለማሳለፍ የሚሞክር ነገር ግን ብልጣብልጦችን በጊዜው ዋጋቸውን የሚከፍል ፈጣሪን የሚፈራ ህዝብ ነው። ለዚህ ህዝብ በመስራትና ለጥያቄው ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ብልጣብልጥ አካሄድ የሚሄዱበት **ካሉ ይመኑኝ መዳን ከሌላ ስፍራ ይሆንለታል።**